Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto
ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ
1910 Kennedy Road, Unit 3, P. O. Box 417, Toronto, ON, M1P 2L8 E-mail: *torontofinote@gmail.com*

# ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከቶውንም ሊረሳውና ሊዘነጋው የማይገባ አደጋ

ኢትዮጵያን ለማጥፋት በቅድሚያ አማራንና የኦርቶዶክስ ኃይማኖትን ማዳከምና ማጥፋት አለብን በማለት የኢትዮጵያ ጠላቶች ሻዕቢያ፣ ሕወኃት/ ወያኔና ኦነግ ሌሎችም የመገንጠል ዓላማን ያነገቡ አንዱ ዓላማቸው አድርገው በወያኔ መሪነት 28 ዓመት ሙሉ ያደረሱት ጥፋት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ የጎሳ ፖለቲካ ውጤቱም ሕዝብ ሲያስጨርስና አገር ሲያጠፋ አይተናል፡፡

ከሶስትና አራት አመት በፊት የሕዝብ አመጽ እያየለ በመምጣቱና የኢትዮጵያ ሕዝብ አልገዛም ብሎ አገዛዙ በተንገዳገደበት ወቅት፤ 'ለውጥ መጣ' ተብሎ ሕዝብን በማዛናጋት ይህንን አገር አጥፊ ስርዓት በነአብይ/ኦዴፓ ተተክቶ የወያኔ ሽማግሌ ሹማምንት መቀሌ ከትመው ረጅሙን እጃቸውን እየዘረጉ አገሪቱን ሲያምሱ ከርመዋል፡፡ በነአብይ አህመድና ለማ መገርሳ ጥሪም ኦነግ ከአስመራ ከነትጥቁ መጥቶ በኦሮሚያ ክልል ከሰራዊቱ ጋር ተደባልቆ የፈረደበትን አማራ 'መጤ' በማለት፣ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዩንም ጨምሮ በኦነግ ሰራዊት በሱማሌ፣ ኦሮሚያ፣ ቤንሻጉልና ደቡብ ክልል ለመስማት እጅግ በሚዘገንኑ ሁኔታዎች ታረደ፣ ተጨፈጨፈ፣ ቤት ንብረቱና ቤተክርስቲያኖች በእሳት ጋዩ፣ ሴቶች ተደፈሩ፣ ቤተሰብ ተበታተነ፣ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ታግተው ደብዛቸው ጠፋ፡፡ በኢ/ያ የህግ የበላይነት ባለመኖሩ፣ ሰራዊቱና ፖሊሱ የሕዝብን ጥቃት የሚከላከልና የሚጠብቅ ኃይል ሳይሆን ቆሞ እያየ የነጃዋርና ኦነግ ሰራዊትን ግድያና ጥፋት 'ቶሎ ቶሎ በሉ' የሚል እንጂ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን የኦፒዶ/ ብልጽግና መሪዎች ወንጀሉን በመካድና 'ግጭት' እያሉ ከማውራት ባሻገር የመሬት ዘረፋ፣ የስልጣን ሽሚያና ሀብት የማግበስበስ ሰራ ላይ ተጠምደው፣ አብይ አህመድ ከተማ በማሳመርና ዛፍ በመትከል፣ እነ ሺመልስ አብዲሳ የኦሮሚያን ልዩ ኃይል በመቶ ሺዎች እያሰለጠኑና እያጠነከሩ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ተወላጆችን 'የተፈናቀሉ' በማለት ወደ አዲስ አበባ በማስመጣት መታወቂያና አፓርትመንት በማደል አዲስ አበባን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ስራ ላይ ተጠምደው ነበር፡፡

አብይ አህመድ እርምጃ የሚወስደው በስልጣኑ ሲመጡበት ብቻ ነው፡፡ ዛሬ እራሱ ወደ መቀሌ ሽኝቶ የከተሙትን የወያኔ ወንጀለኞች ወደ አራት ኪሎ ለመግባት የሚያደርጉትን ግርግር ለስልጣኑ ሰላሰጋው የራሱን የጦር ሹማምንት ወደመቀሌ አዝምቶ እየተታኮሱ ይገኛሉ፡፡ ልብ ልናደረገው የሚገባን ወያኔም ሆነ ኦነግ ጋር በስልጣን ሽኩቻ የሚያደርጉትን ውጊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሙን እንዲያፈስለት እየቀሰቀሰ ይገኛል፡፡ በተለይ አማራወን መሳሪያ እያደረገው ነው፡፡ አብይ አህመድ የወልቃይት ጠገዴን ሁመራና ራያ ጉዳይ ሲጠየቅ ምን ብሎ እንደመለሰ አይዘነጋም፡፡ ሰለሕገ መንግስቱም መለወጥ ሲጠየቅ ጥያቄው ከአማራ ክልል መሪዎች የመጣ ነበርና 'ለአንድ ክልል ተብሎ ሕገ መንግሥት አይቀየርም' ማለቱን የሚረሳ ካለ የዋሕ ሳይሆን ጅል ነው፡፡ የአማራ ክልል መሪዎችን እርስ በእርሳቸው ተገዳደሉ ብሎ ምን አይነት ወንጀል እንደተፈጸመ አይዘነጋም፡፡

ይህ አፈ ቅቤ ልቡ ጩቤ፣ ቀጣፊና ዋሾ አብይ አህመድን ቃል ማመን በተለይ አማራንና ኦርቶዶክስን ቀጥሎም ሌሎችንም ብሄረሰቦች ከመጨፍጨፍ ወደ ኋላ የማይል፣ የአምባገነንነቱን መጠንም አይተን በማናውቀው ሁኔታ እያደገና እየፈረጠመ ሄዶ የኦነግ ን ዓላማ በሂደት ለማሳካት እየሰራ መሆኑን ለደቂቃም ቢሆን መዘንጋት የለብንም፡፡

ትግሉ ይህን ወንጀል በሕዝብና በአገር ላይ የፈጸሙና ያስፈጸሙ ሁሉ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከሶ ማቅረብና ማስቀጣት፤ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋምና አገር አጥፊውን የመንግስት ሕግ በሕዝብ የረቀቀና የጸደቀ ሕገ መንግስት መስርቶ ኢትዮጵያን በዲሞክራሲያዊ ጎዳና መምራት ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውጭ የለም፡፡

ሰለሆነም አማራውም ሆነ ሌላው ኢትዮጵያዊ እነመለስ ዜናዊ የባድመ ጦርነት ጊዜ የሚኒልክና የቲዎድሮስን ፎቶ በየመሸጉ እያደረጉ ኢትዮጵያዊውን ወኔውን በማስነሳት ካሻዕቢያ ጋር በተደረገው ጦርነት 100000 አማራና ኦሮሞ እንዳለቀ ከዘነጋን፤ ዛሬም ከዚያ በባሰና ባስከፊ ሁኔታ ዋጋ እንደሚከፍል በማስተዋል፤ አብይ አህመድም ፍጹም አምባገነን ሆኖ ኢትዮጵያን እንዳልነበረች ከማድረጉ በፊት ራሱንና አገሩን እንዲከላከልና እንዲጠብቅ በሚያመቸው መንገድ እየተደራጀ ትግሉን እንዲያጧጡፍ እናሳስባለን፡፡

ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ትግል ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!